# <u>እማማ ኢትዮጵያ።</u>

የነጻነት ቀንዲል የጥቁሮች አርማ፣
ውድ እናታችን ናት ኢትዮጵያ እማማ።
ብዙዎች ፈልገው ሊያደርጉዋት ቅኝ ግዛት፣
ፈጽሞ አልተሳካም በልጆቹዋ ብርታት።
ከታሪክ ማህደር እንደምንረዳው፣
አብዛኛው ታሪኩዋ ጠላት መመከት ነው።
የታሪክ ጸሐፊዎች የመሰከሩላት፣
እምዬ ኢትዮጵያ ጥሩ ታሪክ አላት።
ልጆቹዋ ቢሆኑም ጠላት አባራሪ፣
ወደፊት አልሄዱም እንደተባባሪ፣
ስለዚህ ሆነዋል የውጪ ተጡዋሪ።
ምንም ብትመደብ ከገናናዎቹ፣
እድገት ለማስመዝገብ አይደለችም ምቹ፣
እንደውም ወርዳለች በጣም ዝቅ ብላ ከተመጽዋቾቹ።
የቀደም ታሪኩዋን በጣም የሩቁን፣
የታሪክ ጸሐፊዎች እንዲያዩት ትተን፣
እስቲ በደንብ  እንይ የቅርብ የቅርቡን።
በዘመነ ዘውዱ ሕዝቡ ቢቸገርም፣
እንዳሁኑ ጊዜ ግራ አልገባውም።
ንጉሡ ተብለው ታዋቂ ገናና፣
ኢትዮጵያን አርገዋል የአፍሪካ መዲና።
ጄኔቭ ኒዎርክ ላይ ስብሰባ ተካፍለው፣
ተማጽነው ነበረ ኢትዮጵያቺን ብለው።
ዙፋን ላይ ሲቆዩ ስልጣኑ ጥሞአቸው፣
አብዮት መጣና ጉድ አደረጋቸው።
ደርግም በለውጥ ስም አብዮት አውጆ፣
ሕዝቡን አደረገው የባዕድ መናጆ።
በስመ አብዮት የመደብ ትግሉ፣
አዳክሞ አስረከበ ለጡት ነካሾቹ አገሪቱን ሁሉ።
ወያኔዎችም መጥተው ቀንቱዋቸው በለስ፣
ከውጪ ኃይላት ጋር ይሞዳሞዳሉ ሀገር ለመቁረስ።
ታሪኩዋን ዝቅ አርገው ወደ መቶ ቤት፣
ሊተኩ ፈለጉ እውነትን በሐሰት።
ሕዝቡንም ከፋፍለው በዘር በሃይማኖት፣
ሲሉት ይሰማሉ እኛ ነን የቆምነው ለልማት ለዕድገት።
ለአስራ ስምንት አመት ሀሰት መደርደር፣
እግዚዎ የሚያሰኝ ነው የሚያነጋግር።
ዓለም ተሻሽሎ በዕድገት ተመንጥቆ፣
አገራችን ቀረች በጎሣ ማነቆ።
ምን ይሆን ምክንያቱ ዘላለም ቁልቁል፣
ያምላክ ቁጣ ይሆን ወይስ የዕድል።
ለማንም አይጠቅምም የዘር ፖለቲካ፣
ትግል ነው መፍትሔው በሕብ እንዲተካ።
የነጻነት ቀንዲል የጥቁሮች አርማ፣
በአደጋ እኮ ላይ ነች ኢትዮጵያ እማማ።

ታሪክ ምስክር ነው ለጠንካራነቱዋ፣
መጫወቻ ሆነች ሲደክም ጉልበትዋ።
ጉልበትዋ ሲደክም ጠላት ሲበረታ፣
በአንድነት ተባብረን እንሁን መከታ፡
እንደዛ ከሆነ ምንም አትረታ።
እምዬን ያላችሁ እንፍጠር ህብረት፣
እንደዛ ሲሆን ነው የሚያፍር ጠላት።
ለኢትዮጵያ የምናስብ ለወገን የቆምን፣
በተግባር እንግለጽ አንድነት ፈጥረን።
ስለዚህ እንስራ በጣም በርትተን፣
መሳለቂያ እንዳንሆን ኢትዮጵያን አጥተን።

ይበልጣል እውነቱ፡

ከጀርመን።